# የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ
## ዋናው ጽሕፈት ቤት
# The Ethiopian Evangelical Church Mekane Yesus
## CENTRAL OFFICE

ሲኖዶሶች — Synods

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አባይ ዳቡስ ሲኖዶስ | Abay Dabus Synod | ማዕከላዊ ሲኖዶስ | Central Synod | ጅማ ቤቴል ሲኖዶስ | Jimma Bethel Synod | ደቡብ ሲኖዶስ | South Synod |
| አዲስ አበባ ሲኖዶስ | Addis Ababa Synod | ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ሲኖዶስ | Central Ethiopia Synod | ማዕከላዊ ሰሜን ኢትዮጵያ ሲኖዶስ | North Central Ethiopia Synod | ዋቤ ባቱ ሲኖዶስ | Wabe Batu Synod |
| አዶላ ገናሌ ሲኖዶስ | Adola Genale Synod | ዳራ ሲኖዶስ | Dara Synod | ማዕከላዊ ምዕራብ ሸዋ ሲኖዶስ | Western Central Shoa Synod | ምዕራብ ጊቤ ሲኖዶስ | West Gibe Synod |
| አማሮና አካባቢው ሲኖዶስ | Amaro & around Synod | ምሥራቅ ጋምቤላ ቤቴል ሲኖዶስ | East Gambella Bethel Synod | ማዕከላዊ ደቡብ ኢትዮጵያ ሲኖዶስ | South Central Ethiopia Synod | ምዕራብ ሲኖዶስ | Western Synod |
| አምባርቾ ብላቴ ሲኖዶስ | Ambaricho Bilate Synod | ጊምቢ ጆርጎ ሲኖዶስ | Ghimbi Jorgo Synod | ማዕከላዊ ደቡብ ሲኖዶስ | South Central Synod | ምዕራብ ጋምቤላ ቤቴል ሲኖዶስ | West Gambella Bethel Synod |
| ቤጊ ጊዳሚ ሲኖዶስ | Beghi Gidami Synod | ሆሮ ጉዱሩ ሲኖዶስ | Horo Guduru Synod | ደቡብ ኢትዮጵያ ሲኖዶስ | South Ethiopia Synod | ምዕራብ ወለጋ ቤቴል ሲኖዶስ | Western Wollega Bethel Synod |
| ብርብር ዲላ ሲኖዶስ | Birbir Dilla Synod | ኢሉባቦር ቤቴል ሲኖዶስ | Illubabor Bethel Synod | ደቡብ ምዕራብ ቤቴል ሲኖዶስ | South West Bethel Synod | የገላና አባያ ሰበካዎች ማስተባበሪያ | Gelana Abaya Parishes Office |
| ማዕከላዊ ጊቤ ሲኖዶስ | Central Gibe Synod | ሰሜን ምእራብ ኢትዮጵያ ሥራ ማስተባበሪያ | North West Ethiopia Coordination Office | ደቡብ ምዕራብ ሲኖዶስ | South West Synod | ሰሜን ሥራ ክፍል | North Area Work |


ቁጥር
Ref. No. G01/2001/6526/18

ቀን
Date [illegible] 16 [illegible] 2018

**Doc # 2**

**የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ**

**የሚሲዮንና ስነመለኮት ቦርድ**

**ሲመተ-ሐዋሪያንና ሲመተ-ነቢይን በሚመለከት ለቤተክርስቲያኒቱ 18ኛው የሥራ አስፈጻሚ ቦርድ የቀረበ የሥነመለኮታዊ አቋም አስተያየት**

***ታህሳስ 14 -18 2003 ዓ.ም***

እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከ1980ዎቹ አስቶ መሠረቱን ሰሜን አሜሪካ በማድረግ ወደሌሎች አገሮች በፍጥነት እየተስፋፋ ያለው አዲሱ የሲመተ ሐዋሪያ ንቅናቄ ( The New Apostolic Movement ) አድማሱን ቀስ በቀስ በማስፋት እስከ አገራችንም ድረስ ገፍቶ መግባቱ በአብያተ ክርስቲያናትና በተለያዩ ደረጃዎች አነጋጋሪ የስነመለኮት መነጋገሪያ እየሆነ ያለና በምእመናን ዘንድ ከፍተኛ ጥያቄና ብዥታ እየፈጠረ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ ይህንን ጉዳይ በሚመለከት በራስዋ ምእመናንና በሌሎችም ለሚነሱት ጥያቄዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ፤ ከስነመለኮትና ከታሪክ እይታ አቅጣጫ ተገቢውን ምላሽ መስጠትና የረስዋንም አቋም ይፋ ማድረግ የሚጠበቅባት ነው፡፡

ይህንኑ ዓላማ ለማሳካት ይቻል ዘንድ በጉዳዩ ዙሪያ ሥነመለኮታዊ ጥናት እንዲያደርግ አንድ የሥነመለኮት ምሁራን ቡድን ተመድቦ፤ ቡድኑም ላለፉት ጥቂት ወራት በብርቱ ሲሰራበት ቆይቶአል፡፡ ሚስዮም ቡድኑ ያቀረበውን ጥናታዊ ጽሑፍ መሰረት በማድረግ የቤተክርስቲያኒቱ ምላሽና አቋም ይሆናል ብሎ ያመነበትን ሐሳብ እነሆ እንደሚከተለው በአክብሮት ያቀባል፡፡

**ታሪካዊ ቅኝት ( Historical insight):**

1. ከጥንት የቤተክርስቲያን አባቶች ዘመን ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው የቤተክርስቲያን አገልግሎትና አመራር ሶስት የአገልግሎት መደቦች ሲኖሩት እነሱም ጵጵስና ( Bishop) ወይም ክህነት ( Priest)፤ ሽምግልና ( Presbyteros); እና ድቁና ( Deacon ) ናቸው፡፡ እነዚህ የአገልግሎት መደቦች ሐዋሪያዊ መሠረት ያላቸው ናቸው፡፡ በዘመነ ሐዋሪያት የነበረው የቤተክርስቲያን አመራርና የወንጌል አገልግሎት በያንስ እስከ አንደኛው መቶ ክፍል

ፖ.ሣ.ቁ. 2087
P.O.Box 2087

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

Tel: (+251-115) 533293
Fax: (+251-115) 534148
E-mail: eecmyco@eecmy.org

ዘመን ማገባደጃ ሐዋሪያው ጳውሎስን ጨምሮ በሐዋሪያቱና እነሱ በየአጥቢያው በሾሙአቸው ሽማግሌዎችና ወንጌላዊያን እንዲሁም መጋቢዎች ይከናወን ነበር፡ ዘመነ ሐዋሪያቱ ከተጠናቀቀ በኋላም ጳጳሳት ( Bishops) የሐዋሪያቱን የአመራርና የወንጌል ስብከት ኃላፊነት ተረክበው እየመሩ እስከ ዛሬ ይኸው ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ ቤተክርስቲያን እንደ አንዲት የክርቶስ አካል ህያውነትዋንና አንድነትዋን በሐዋሪያቱ መሠረት ላይ በመጠበቅ እያገለገለች ኖራለች[1]። ይህም እንደየአካባቢው አቢያተ ክርስቲያናት ሁኔታና እንደየባህሉ ለበርካታ ዘመናት ሊቀጥል ችሎአል።

2. በጊዜ ሂደት ግን የሮማ ካቶሊካዊት ቤተክርሰቲያን በማቴ 16፡ 18 ለጴጥሮስ የተባለውን በተዛባ መስመር በመተርጎም የእረኝነትና የወንጌል አስተማሪነት ተልእኮ የነበረውን የጵጵስና አመራር በሐዋሪያነት ትኪ ( Apostolic Succession ) አቅጣጫ በማዋቀር አመራሩ ምዕመናንን እንደየቦታወና እንደየማህበራዊ አውዱ ከማገልገል ይልቅ ወደ ዓለም አቀፋዊ ወይም ጠቅላይ የአገዛዝ ሥልጣን እንዲቀየር አደረገች።

3. ከዚህም የተነሳ በተለይ በምእራቡ ክፍል የነበረችው ቤተክርስቲያን በሚሲዮናዊ አገልግሎትዋ ሳይሆን በመንግስታዊ ዓይነት የአገዛዝ ገጽታዋ እንድትታወቅ አደረጋት፣ አገልግሎትዋም ፍቅርን፣ እረኝነትን፣ ትህትናን ፣ እምነትን፣ ቃሉን እና ጸጋውን መሠረት ያደረገ መሆኑ ቀርቶ በሰብአዊ አስተሳሰብና ውሳኔ ብቻ የሚከናወን ሆነ። ይህም በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በነማርቲን ሉተር ለተመራው የቤተክርስቲያን ተሃዲሶ እንቅስቃሴ ዋነኛ መነሻ ሊሆን ችሎአል።

**ጥንታዊውን የዘመነ ሐዋሪያት አሠራር መልሶ የማዋቀር እንቅስቃሴ**
*(Apostolic Restoration Movement )*

4. የዘመነ ሐዋሪያትን አሠራር መልሶ የማቋቋም እንቀስቃሴ ፣ በጥንትዋ ቤተክርስቲያን የነበረው መንፈሳዊ አመራርና የአገልግሎት አሠጣጥ ያኔ በነበረ መልኩ ዳግም እንዲመሠረት የማድረግ ዓላማን የያዘ ንቅናቄ ነው። የዚህ እንቅስቃሴ አጀማመር በተለይ በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መገባደጃ አካባቢ "The **Stone-Campbell Movement**" በሚል ስያሜ ከሚታወቀው "ታላቁ ዳግማዊ መነቃቃት" (Second Great Awakening) ጋር የተያያዘ መሆኑን የሃኛው መቶ ክፍለ ዘመን ቤተክርሰቲያን ታሪክ ያስገነዝባል። ይህ እንቅስቃሴ ራሱን ከጥንትዋ ቤተክርስቲያንና ከሐዋሪያቱ መዋቅር ጋር በቀጥታ ለማስተሳሰር ጥረት ያደርጋል፣ ዋነኛው ግቡም የዘመነ ሐዋሪያት መልክ ያለውን አመራርና አሠራር ወይም መደበ አገልግሎት በመፍጠር ክርስቲያኖችን ሁሉ በአንድ አካል ስር መጠቅለል ነው ( *Unification of all Christians in a single body patterned after the Church of the New Testament* )[2]

5. ይህ እንቅስቃሴ በአሁኑ ጊዜ "***International Coalition of Apostles***(ICA)" , በመባል የሚታወቅ ማህበር ነክ አወቃቀር ያለው ቢሆንም ከጊዜ ወደ ጊዜ ሲከሰቱ ከነበሩት የውስጥ መከፋፈል የተነሳ ስያሜው እየተለዋወጠ ከመኖሩ አቅጣጫ ሲገመገም በዚህ ስያሜ የመቀጠሉ ሁኔታ ሊያጠራጥር ይችላል። ለምሳሌ ቀደም ሲል በሰሜን አሜሪካ በአንድ ስያሜ ሲንቀሳቀስ የነበረው አዲሱ የተሃድሶ ንቅናቄ በኋላ ላይ <u>የክርስቶስ አቢያተክርስቲያናት</u> ( Churches of Christ ) ፣ <u>የነጻይቱ ቤተክርስቲያን ማህበር</u> (The Independent Christian Church ) ፣ <u>የክርስቲያን ቤተክርስቲያን</u> ( Christian Church ) እና የመሳሰሉትን ስያሜዎች በመያዝ

---

[1] Paul M. Dawley ( 1963): Chapters in Church History, Seabury Press, New York; p 40

[2] www: apostolicrestoration.org

መከፋፈሉ ይታወቃል[3]:: ይሁን እንጂ ብዙም እነዚሁ ራሳቸው ብዙም ሳይቆዩ ስነመለኮታዊ አቅጣጫዎቻቸውን በመቀየር ከላይ የተጠቀሱት ሶስቱ ክፍሎች ዳግም በመዋሐድ " Christian Connection" ራሳቸውን እንደገና ለማደራጀት ጥረት አድርገዋል[4]::

6. አንዳንድ የቤተክርስቲያን ታሪክ ዘጋቢዎች የRestoration ንቅናቄ ታሪክ የሚጀምረው ከመካከለኛው ዘመን የተሃድሶ እንቅስቃሴ ማለትም ከነጆን ዊክሊፍ እና ጆን ሁስ ነው የሚል ሐሳብ አላቸው:: በእርግጥ እነዚህ ሁለቱ የተሃዲሶ ጀማሪዎች በመካከለኛው ዘመን በነበረችው ቤተክርስቲያን ይታይ የነበረውን የቅድስና ጉድለትና ዓለማዊነት፤ በተለይም ለእግዚአብሔር ቃል ይሰጥ የነበረውን ዝቅተኛ ግምት በመቃወም ነበር ራሳቸውን መስዋእት ያደረጉት:: የቤተክርስቲያንን መሠረታዊ ክርስቲያናዊ እውነትና ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን የተቀደሰ አሠራር የመቀየር ዓላማ አልነበራቸውም፤ ትግላቸው ከዩውንም የዘመነ ሐዋሪያትን አሠራር መልሶ የማቋቋም ዓላማ አልነበረውም[5]::

7. ከፍ ሲል የተጠቀሱት እንቅስቃሴዎች በባህሪይአቸውም ሆነ በአመለካከታቸው ይለያያሉ:: ቢሆንም በሥነመለኮታዊ መሠረታቸው ተመሳሳይነት አላቸው:: ክስቶን ካምቤል እንቅስቃሴ ጀምሮ እስከዛሬ ከተሰሙት ሥነመለኮታዊ እንደምታ ያላቸው ሲያሜዎች መካከል Post Denominationalism, kingdom Now Theology; Reconstructionism; the Later Rain Movement, Manifest Sons of God; Joel's Army; The New Thing; The Third Wave የሚባሉት ዋነኞቹ ነበሩ:: እነዚህ በስያሜ ወይም በስነመለኮት አባባል የተለያዩ ይሁኑ እንጂ ሁሉም የጥንቱን መመለስ በሚል ዓላማ ይስማማሉ:: በተጨማሪም የመጨረሻው ዘመን መጨረሻ ስለተቃረበ ቤተክርስቲያንን ወደቀደመው ማንነትዋ ለመመለስ ልዩ መንፈሳዊ ጥበብ የተካኑ መሪዎች ያስፈልጋሉ ባዮች ናቸው:: ምናልባት የመካከለኛው ዘመን የጠቅላይ አገዛዝ ዓይነት ሥርዓት በዚህ ዘመን መልኩን ቀይሮ ራሱን ይደግም ይሆንን?

## አዲሱ የዘመነ ሐዋሪያ መላሽ እንቅስቃሴ

8. አዲሱ የዳግማዊ ዘመነ ሐዋሪያ እንቅስቃሴ ምንጩ ከፍ ሲል ከተዘረዘሩት መካከል በተለይ ከፖስት ዲኖሚኔሽናልዝም እንቅስቃሴ ጋር የተያያዘ ነው:: የዚሁ እንቅስቃሴ አካል ሆኖ እያለ በኋላ ላይ ፒተር ዋግነር የሚባል የአዲሱ እንቅስቃሴ መሪ ሌላ ስያሜ ሰጥቶት እስካሁን"New Apostolic Reformation" በሚል ቀጥሎአል:: እንደዋግነር አባባል ይህ አዲስ ስያሜ በ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ባለችው ቤተክርስቲያን ሐዋሪያዊ ሥልጣን እንዲንሰራፋ በማድረግ ልዩና ወሳኝ የመጨረሻ ዘመን ተሃድሶን እውን ማድረግ ነው::

9. ከ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አንስቶ መልኩን እየለዋወጠ በመስፋፋት ላይ ያለው የሲመተ ሐዋሪያና ሲመተ ነቢይ እንቅስቃሴ ሥነመለኮታዊ አመለካከት የፍጻሜን ወይም የሙላትን ( Eschatological ) ጽንሰ ሐሳብ መሰረት ያደረገ ነው:: ይህም መጨረሻው ዘመን ስለተቃረበ ቤተክርስቲያንን ወደ ፍጹምነት ለመመለስ ልዩ መንፈሳዊና ሐዋሪያዊ አመራር ያስፈልገዋል፤ ይህም ከቅስና አመራር ስር ቤተክርስቲያንን በማላቀቅና አዲሶቹን ሐዋሪያት የቁሶች አለቃ የማድረግ ግብ አለው::

---

[3] www.toddtyszka.com/newaposrest.html

[4] IBD; p 1023

[5] Kenneth S. Latourette ( 1953): History of Christianity, Harper Brothers Publishing, New York Pp 666-673

10. የዘመናችን እንቅስቃሴ ለቀደሙት የተሃዲሶ እንቅስቃሴዎች በተወሰነ ደረጃ እውቅና ይሰጣል። ለምሳሌ ማርቲን ሉተር የመካከለኛውን ዘመን ቤተክርስቲያን ስህተት በማጋለጥ በዘመነ ሐዋሪያት የነበሩትን የደህንነት ተምህርቶች ወይም የደህንነት መንገዶች ማለትም ጸጋው ብቻ፤ ቃሉ ብቻ፤ እምነት ብቻ በሚል የሚታወቁትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች ከተረሱበት ወይም ከተጣሉበት አንስቶአቸዋል ( Restored )። ስለዚህ አዲሶቹ የዳግመ ሐዋሪያ እንቅስቃሴ መሪዎች የዘመናችን ሉተሮች ናቸው ማለት ነው። ይህንን ሐሳብ ፒተር ዋግነር በአንድ አጋጣሚ አስምሮበታል[6]። ሆኖም የአዲሱ እንቅስቃሴ ተሃዲሶ ማርቲን ሉተር ካደረገው በላቀ መልኩ ሥር ነቀል ነው፤ ሉተር የጀመረው አሁን ይጠናቀቃል ባዮች ናቸው።

11. ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው አዲሱ የዘመነ ሐዋሪያት እንቅስቃሴ የራሱ ማህበርተኞች አሉት። ከማህበርተኞቹም መካከል አንዳንድ ታዋቂ የአገራችን ዜጎች እንደሚገኙ ይታወቃል፤ ከነርሱም የሐዋሪያነት ሹመት የተሰጣቸው እንዳሉ ግልጽ ነው። የማህበሩ ዓላማ በዓለም ሁሉ የሐዋሪያዊ አመራርን መዋቅር መዘርጋት ስለሆነ በየአገሩ የበላይና የበታች ዓይነት ሐዋሪያት እንዲሾሙ በማድረግ ላይ ይገኛል[7]። በአገራችንም ሲመተ ሐዋሪያንና ሲመተ ነቢይን በሚመለከት ጥያቄዎች መነሳት የጀመሩት ከዚሁ እውነታ ነው።

<u>ጥንታዊውና እውነተኛው ሐዋሪያዊ ተልእኮ በክርስቶስ በተደረገው ቀጥታ ጥሪና ሹመት ላይ የተመሰረተ ነው በሰው በኩል በሆነ ትንቢታዊ ማረጋገጫ አልነበረም</u>

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ ሲመተ ሐዋረያንና ሲመተ ነቢይን በሚመከት ያላት አቋም በሚከተሉት ስነመለኮታዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሐሳቦች ላይ የተመሰረተ ይሆናል።

*1. አምስቱ ጣምራ የአገልግሎት መደቦች*

12. በመጀመሪያ "አምስቱ ጣምራ የአገልግሎት መደቦች" የሚለውን አባባል አግባብነት መመልከት ተገቢ ነው። እንደሚታወቀው ብዙዎች በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በኤፌ 4፡11 ላይ የተዘረዘሩትን አገልግሎቶች በመደበ አገልግሎትነት (offices of Ministry) ይጠቅሱአቸዋል። ነገር ግን በሐዋሪያው ጳውሎስ የነበረው ሐሳብ አገልግሎቶቹ ላይ እንጂ በአገልግሎት መደቡ ላይ ያረፈ አልነበረም። ይህንን በትክክል ለመገንዘብ ይቻል ዘንድ የኤፌሶንን መልእክት ማእከላዊ ሐሳብ ( Theme) እና አውድ ( Context) መረዳት ተገቢ ይሆናል።

13. የኤፌሶን መልእክት ማዕከላዊ ሐሳብና ዓላማ የቤተክርስቲያን አንድነትና የቤተክርስቲያን ውስጣዊ እድገት ነው። ከምዕራፍ 1-2 ያለው የደህንነት ምስጢር ላይ ያተኮረ ሲሆን ይህ ደህንነት በእግዚአብሔር ዘንድ የነበረው ዘላለማው ሐሳብ በክርስቶስ አማካይነት በአስደናቂ ሁኔታ መፈጸሙ ሲሆን ቤተክርስቲያን በአህዛብ መካከል መፈጠርዋ ራሱ እግዚአብሔር ለዓለም ሁሉ የነበረውን ዘላለማዊ እቀድ የሚያመለክትና ይህም አሰራር የማይገናኙትን አይሁድና አህዛብ የሚባሉትን በክርስቶስ በአንድነት መጠቅለሉ ነው። በዚህም ቤተክርስቲያን ተፈጠረች። ከዚህ ልዩ ልዩ ከሆኑት አንዲህ ዓይነት ወገኖች የተፈጠረችውና አንዲት አካል የሆነችው ቤተክርስቲያን ግን በክርስቲያናዊ መረዳትና በምሳሌያዊ ህይወት ማደግ ይጠበቅባታል። እድገቱ ደግሞ ክርስቶስንና ምስጢሩን በጥልቀት በማወቅ ላይ የሚመሠረት ነው። እድገቱ ግን መሠረት አለው፤ መሠረቱም በኤፌ 2፡ 20 ላይ የተገለጸው

---

[6] Cindy Jacobs National School of the Prophets--Mobilizing the Prophetic Office, May 11th 2000--Quoted in Www.apostletoddtyszka.com.

[7] Please refer to the main study paper

*ነው---በሐዋሪያትና በነቢያትም መሠረት ላይ ታንጻችኋል፤ የማእዘኑም ራስ የሆነው ድንጋይ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።*

14. ኤፌ 4፡11 የሚተረጎመውም በምዕ 2፡20 እይታ ውስጥ ነው። ኤፌ 2፡ 20 ፤ 3፡ 5 በተጣለው መሠረት ላይ ያሉትን አገልግሎት የሚመለከት ነው። መሠረቱ ተጥሎአል፤ ገና የሚጣል አይደለም። የኤፌ 4፡11 ዓላማ ቤተክርስቲያንን ወደ ክርስቶስ ሙላት የሚያሳድጉትን አገልግሎቶች ለማመለክት ነው። እነዚህም አገልግሎቶች የውስጥና የውጭ ናቸው። ሐዋሪያት የሚለው የቤተክርስቲያንን ሚሲዮናዊ ኃላፊነት የሚያስገነዝብ ነው። ሐዋሪያ የሚለው የአማሪኛ አባባል በግሪኩ አፖስቶሎስ የሚል ሲሆን አፖስቶሎስ ማለት ደግሞ የሚላክ ማለት ነው። ይህ ተንቀሳቃሽ ( Itinerant ) ወንጌላዊያንን ማለትም እንደነፊሊጶስ ዓይነት ያሉትን የሚያመለክት እንጂ የዘመነ ሐዋሪያት ዓይነት ሐዋሪያዊ ሥልጣን ቀጣይነትን የሚያመለክት አይደለም። ነገር ግን እነዚህ አገልግሎቶች ቋሚ የቤተክርስቲያን አገልግሎቶች ናቸው፤ የቤተክርስቲያን ማንነትም በነዚሁ ይገለጸል። የተቀሩት አራቱ የአገልግሎት ዓይነቶችም በዚሁ መልክ ሊተረጎሙ ይችላሉ---ይህንንም እንደሚከተለው በአጭሩ ማስቀመጥ ይቻላል። በጥቅሉ፤ ኤፌ 4፡11 አምስት መንገዶች ያሉት የአንዱ አገልግሎት አፈጻጸምን ያስገነዝባል። ለምሳሌ ያህል እጅ እጅ ተብሎ ይጠራል፤ ግን በአምስቱ ጣቶች አማካይነት ተግባሩን ያከናውናል። አምስቱ ጣምራ አገልግሎቶችም እንደዚሁ የአንዱ አገልግሎት መውጫዎች ናቸው ማለት ይቻላል።

1. **አፖስቶሎስ** ( የወንጌል መልእክተኛ) ፡ በኤፌሶን አውድ ውስጥ ሲታይ አፖስቶሎስ በቤተክርስቲያን ተልከው በየቦታው ወንጌል በመስበክ ማህበራነ ምእመናንን ( አጥቢያ ቤተክርስቲያንን) የሚመሰርቱ፤ መሪዎችንም ለማህበሩ የሚሾሙ ናቸው።

2. **ፕሮፌታስ** ( ነቢያት/ የትንቢታዊ መልእክት አገልጋዮች)፡- የትንቢታዊ መልእክት አገልጋዮችም ተልእኮአቸው የሚያመዝነው የደህንነቱን መንገድና የእግዚአብሔርን ሐሳብ ለህዝብ በማሳወቅ ላይ ነው። አገልግሎቱ በመደበኛነት በማህበረ ምእመናን ( በአጥቢያ ቤተክርስቲያን) የሚከናወን ወይም ልክ እንደአፖስቶሎስ ከቦታ ወደ ቦታ የሚያንቀሳቅስ ሊሆን ይችላል።

3. **ኢቫንጌሊስታስ** ( ወንጌላዊያን)፡- ማእከላቸውን ማህበረ ምእናን ( አጥቢያ ቤተክርስቲያን) በማድረግ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ከቦታ ወደ ቦታ እየተንቀሳቀሱ ስለክርቶስና ስለአዳኝነቱ የሚመሰክሩ እና የሚያጠምቁ አገልጋዮች።

4. **ፖይሜናስ** ( እረኞች/መጋቢዎች/ቄሶች )፡- የእረኝነት አገልግሎት በማህበረ ምእመናን የሚከናወን ሲሆን በዚህ አገልግሎት ላይ የሚሾሙት ማህበሩን በማስተዳደር ፤ ከቀን ወደ ቀን የምእመናንን ህይወት የሚከታተሉ ፤ የሚመክሩና የሚያስተምሩ ፤ እምነቱንም የሚጠብቁና የሚያስጠብቁ ናቸው፡

5፡ **ዲዳስከሎእ** ( አስተማሪዎች) ፡ የበአንድ ማህበረ ምእመናን በቋሚነት ተሹመው ቃሉን በመተርጎም እና መሰረታዊ ዶክትሪንን በማስተማር ምእመናንን በእምነት የሚያሳድጉና ለዚህም የጸጋ ሥጦታ ያላቸው ናቸው።

15. በጥቅሉ ስንመለከት ኤፌሶን 4፡11 ቤተክርስቲያንን ቤተክርስቲያን የሚያሰኙ አገልግሎቶችን የሚያመለክት ሲሆን በነዚህ አገልግሎቶች ምክንያት ቤተክርስቲያን ውስጣዊና ውጫዊ እድገት ይኖታል። ክፍሉ ስለአገልግሎት መደብ ( Office of Ministry) ሳይሆን በቤተክርስቲያን ሊኖር ስለሚገባ የተሟላ አገልግሎት ( function) የሚናገር ነው።

በተጨማሪም የሥልጣንና የበላይነት መዋቅርን ሳይሆን የአገልግሎቱን ምሉእነትና በአካሉ አንድነት ውስጥ በፍቅር ሊከናወኑ የሚገባቸውን ተግባራት የሚያመለክት ነው።

16. የአዲሱ የስመ-ሐዋሪያት እንቅስቃሴ መሪዎች ከፍ ሲል በተጠቀሱት ስነመለኮታዊ እና ስነቤተክርስቲያን አመለካከታቸው ምክንያት የዘመነ ሐዋሪያት አሠራር ዳግም መመለስና መቋቋም አለበት ይላሉ። ስለዚህም ዛሬ በየአገሩ የሚሾሙት የአዲስ ሲመተ ሐዋሪያት እንቅስቀሴ ሐዋሪያት ከጥንቶቹ ሐዋሪያት ጋር የተካከለ ሥልጣንና ብቃት አላቸው የሚል አዝማሚያ ይታይባቸዋል።

17. ይህ አስተሳሰብ የተሳሳተ ስለመሆኑ በቂ መጽሐፍ ቅዱሳዊና ታሪካዊ እውነቶች አሉ። በመጀመሪያ ደረጃ መጽሐፍ ቅዱስ ስለሐዋሪያት ጥሪና አሸዋሾም የሚያስተምረውን መመልከት ይገባል። ይህንንም ከታች በዝርዝር እንመለከታለን፦

   1. ቀዳሚው የሐዋሪያነት መመዘኛ በክርስቶስ በራሱ ቀጥታ መጠራትና መሾም፤ እና መላክ ነው። ጌታ ኢየሱስ አስራ ሁለቱን በቀጥታ ጠርቶ ሾማቸው፤ ላካቸውም። በሉቃ 6፡13 ላይ ይህ ጉዳይ በተሻለ ግልጽነት ተመዝግቦ እናገኛለን *፡ በነጋም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን ጠራ፤ ከነርሱም አስራ ሁለቱን መረጠ፤ ደግሞም ሐዋሪያት ብሎ ሰየማቸው ፡፡*

   2. የክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ ፤ እንዲሁም የእርገቱ የዓይን ምስክር መሆን ሌላኛው የሐዋሪያነት መመዘኛ ነው። በወንጌላቱ ተጽፎ እንደሚገኘው ደቀ መዛሙርቱ ( ሐዋሪያቱ) የክርስቶስን ሞትና ትንሳኤ በቅርብ ወይም በቅርብ ርቀት መስክረዋል። ከትንሳኤ በኂላ ጌታ ኢየሱስ እነዚህኑ ዳግመኛ ወደራሱ ጠርቶ የራሱ መልእክተኞች ሆነው ወንጌል እየሰበኩ ቤተክርስቲያንን እንዲመሰርቱ እንዲህ ሲል ሾሞአቸዋል፡

- "አብ እንደ ላከኝ እኔ ደግሞ እልካችሁአለሁ" ( ዮሐ 20፡21) ፤
- እንግዲህ ሂዱና አህዛብን ሁሉ በአብ፤በወልድና በመንፈስ ቅዱስ እያጠመቃችሁአቸው፤ ያዘዝሁአችሁንም እንዲጠብቁ እያስተማራችሁአቸው ደቀ መዛሙርት አድርጉአቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእናንተ ጋር ነኝ ( ማቴ 28፡19-20)።
- ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ ----- ( ማር 16፡ 14 )
- ጌታ ኢየሱስም ከነርሱ ጋር ከተነጋገረ በኂላ ወደ ሰማይ አረገ ፤ በእግዚአብሔርም ቀኝ ተቀመጠ እነርሱም ወጥተው በየስፍራው ሁሉ ሰበኩ ( ማር 16 ፡ 19-20)
- ወደ ዓለም እንደ ላክሽኝ እንዲሁ እኔ ወደ ዓለም ልክኂቸው፤ እነርሱም ደግሞ በእውነት የተቀደሱ እንዲሆኑ እኔ ራሴን ስለ እነርሱ እቀድሳለሁ ( ዮሐ 18፡ 18-19)
- ልትሄዱና ፍሬ ልታፈሩ፤ ፍሬአችሁም ሊኖር ሾምኂችሁ ( የሐ 15፡16ለ)። ፍሬ ልታፈሩ የሚለው ቃል የወደፊት አገልግሎታቸው ልዩ ልዩ ውጤትን የሚያመለክት ቢሆን በዋናነት ሊጠቀስ የምትችለው ግን በምስክርነታቸው መሠረት ላይ የሚትተከል ቤተክርስቲያን ነች፤
- ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፤ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ፤ በሰማሪያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ። ይህንም ከተናገረ በኂላ እነርሱ እያዩት ከፍ ከፍ አለ፤ ደመናም ከዓይናቸው ሰውራ ተቀበለቻቸው ( የሐዋ 1፡ 6-9)

18. ከላይ ከተዘረዘሩት እውነታዎች መገንዘብ የሚቻለው የሐዋሪያነት ሹመት በጥቅሉ የመስራችነት ሹመት መሆኑን ነው ይቻላል። በዚህም ምክንያት የዘመኑ ሲመተ ሐዋሪያት ቴኦሎጊ ሐዋሪያን ሐዋሪያ የሚያሰኘው ሥረ-መሠረታዊነቱ ( Authenticity ) መሆኑንም የሚክድ ወይም ግንዛቤውን ያጣ ነው ማለት ይቻላል።

19. *ሥረ-መሠረታዊያኑ ሐዋሪያት* 12 እንደሆኑ ( አስራ አንዱንና ይሁዳን የተካውን ማቲያስን ጨምሮጌታ) ይታወቃል፡፡ ነገር ግን ሐዋሪያ ጳውሎስም በደመስቆ መንገድ ላይ ጌታ ተገልጦለት የአህዛብ ሐዋሪያ እንዲሆን በጌታ በቀጥታ የተሾመ በመሆኑ ከመሰረታዊያኑ ሐዋሪያት ተርታ ይመደባል፤ እርሱም ይህንን በግልጽ መስክሮአል ( ገላ 1:12 ፤ 1ቆሮ 15: 3-10)፡፡ *በመጨረሻ ከሁሉ ለማንስ ለኔ ደግሞ ታየ* የሚለው ቃል በአንድ በኩል የጳውሎስን ትህትና የሚያመለክት ሲሆን በሌላ መልኩ ግን የትንሰኤው ምስክሮች ከሆኑት ሐዋሪያት በኂላ መጠራቱንና ከእርሱ በኂላ ሌሎች ሐዋሪያት አለመኖራቸውን የሚያስገነዝብ ነው፡፡

20. ይህንን ጉዳይ ከሥነመለኮት አንጻር መመልከት ይቻላል፡፡ ለግንዛቤም ይሆን ዘንድ የመንፈስ ቅዱስን መውረድ እንደማነጻጸሪያ ( Analogy) መጠቀም አስፈላጊ ይሆናል፡፡ እንሚታወቀው የጴንጤቆስጤ በዓል አይሁዳዊ በዓል ነበር፤ መንፈስ ቅዱስ በዚህ ዕለት በመውረዱ ምክንያት ወንጌላዊያን ተርጓሚዎች ( በተለይም ከሚሲዮሎጂ አንጻር) በበዓለ ሃምሳ የተከሰተው መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ኢየሩሳሌምን መሠረት ያደረገና የቤተክርስቲያንን መመስረት ያበሰረ ነው፡፡ ኢየሩሳሌምም የተስፋው ፍጻሜ ማዕከል ( Eschatological fulfillment) በመሆንዋ ይህ እጅግ አስፈላጊ ነበር፡፡

21. ነገር ግን ይህ የአይሁድ ጴንጠቆስጤ የአህዛብም ይሆን ዘንድ መንፈስ ቅዱስ በአህዛቡ ማዕከል በቂሳሪያ በነበሩት ወገኖችም ላይ ወረደ፡፡ የቂሳሪያው የመንፈስ ቅዱስ መውረድ የአህዛብ ጴንጤቆስጤ ሊባል ይችላል፡፡ መንፈሱ ግን አንድ ነው፡፡ የዚህ መንፈስ አንድነት በቅርብ ያሉትን አይሁድና ርቀው የነበሩትን አህዛብ በክርስቶስ አንድ አደረጋቸው--ከዘለዓለም ዓለም ጀምሮ በእግዚአብሔ ዘንድ የነበረው የቤክርስቲያን አንድት ሐሳብም እውን ሆነ ( ኤፌ 1-3)፡፡ ስለዘህ ነው የኤፌሶን መልእክት ጭብጥ ወይም መሰረታዊ ዓላማ የቤተክርስቲያን አንድነትና ህይወትዋና ምስክርነትዋ ላይ ያተኮረ ነው የምንለው፡፡ በዚህ ሥነመለኮታዊና ስነትርጉማዊ አካሄድ ሲታይ ጳውሎስ የአህዛቡን ወገን የሚወክል ሐዋሪያ ነው--ስለዚህም የጳውሎስ ሐዋሪያነት የእግዚአብሔርን መንግስትና የመንግስቱን መልእክት አንድነት ያመለክታልና አጠራሩ መለኮታዊ ነው፡፡ ስለዚህም ጳውሎስ የሐዋሪያነት መስፈርት የሚያሟላ መሆኑ አያጠራጥርም፤ ከርሱ በኂላ ግን ቀጣይ ሹመት ስለመኖሩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምስክርነት የለም፡፡

22. ከመሠረታዊያን ሐዋሪያት ጋር የማይቆጠሩ ነገር ግን ሐዋሪያት ተብለው ይጠሩ የነበሩት ሌሎችም እንዳሉ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ የሐዋሪያነት ስያሜ እንጂ የሐዋሪያነት ጥሪና ሹመት የተሰጣቸው ስላልሆነ ሐዋሪያነታቸው ሥረ-መሠረታዊነት ( Authenticity ) የለውም፤ የነርሱ በዚህ ስያሜ መጠራትም የሲመተ-ሐዋሪያን ቀጣይነት አያመለክትም፡፡ ከነዚህ መካከል እንደ ምሳሌ ሊጠቀሱ የሚችሉት በርናባስ ( የሐዋ 14:14)፤ አንድሮኒቆን እና ዩሊያን ( ሮሜ 16 ፤ 7 ) ናቸው፡፡ ምናልባት በጊዜው እነዚህ አገልጋዮች እነጳውሎስን ከመሳሰሉ ሐዋሪያት ጋር በቅርብ ከማገልገላቸውና ከሐዋሪያነቱ ያላነሰ መንፈሳዊ ብቃት የነበራቸው ከመሆኑ የተነሳ ምእመኑ የሐዋሪያነት ስያሜ ሰጥቶአቸው ሊሆን ይችላል፡፡ ጳውሎስም ቢሆን እነዚህን ሐዋሪያት ብሎ ሲጠራቸው መልእክተኝነታቸውንና በሐዋሪያት መሠረት ላይ ቤተክርስቲያንን እያነጹ መሆናቸውን ለማመልከት ካልሆነ በስተቀር ሐዋሪያት መሆናቸውን በይፋ ለማስተዋወቅ አልነበረም፡፡ እንዲህ ቢሆን ኖሮ በገላቲያ 1 ላይ ስለባርናባስ ሲጠቅስ ሐዋሪያው በርናባስ ብሎ ሊጠራው ይችል ነበር፡፡

23. ሐዋሪያነት በየትኛውም መልኩ ከሰው ሊሰጥ የሚችል ሹመት ሊሆን አይችልም፡፡ ከላይ እንደተመለከትነው፤ ጠሪውም ሸዋሚውም ጌታ ኢየሱስ ነበር፡፡ ለክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ የዓይን ምስክር የሆኑት 12ተና ክርስቶስ በመለኮታዊነቱ ቀጥታ የተገለጠለትና የሾመው ጳውሎስ ብቻ በሐዋሪያነት ይታወቃሉ፡፡ ስለዚህም የአዲሱ ሲመተ-ሐዋሪያት እንቅስቃሴ በትንቢት ወይም በሰው ጥሪ ወይም ጥቆማ ወይም በቤተክርስቲያን ውሳኔ ፤ ወይም በማህበር የሚፈጸመው

አደራረግ ፈጽሞ መሠረቱን የለቀቀ ሰብአዊ አሠራር ነው። በመሠረቱ የአዲሱ ሲመተ ሐዋሪያ እንቅስቀሴና ሲመተ ነቢይ እንቅስቃሴ የተጣመሩ ናቸው--ሐዋሪያቱ ነቢያትም ሐዋሪያትም ናቸውና--አንድም ሁለትም ናቸውና አይለያዩም። ሁለቱም የRestoration ንቅናቂ አካል ናቸው።

24. ከዘመነ ሐዋሪያት ማብቂያ በኋላ ቀኖና መዘጋቱ ይታወቃል። የቀኖናው መዘጋት የቤተክርስቲያን ሐዋሪያዊና ነቢያዊ መሠረት የመጣሉ ተልእኮ መጠናቀቁን ያመለክታል። ስለዚህም ከቀኖናው መዘጋት በኋላ ቤተክርስቲያን የምትኖረው ሐዋሪያቱና ነቢያቱ ባስተላለፉትና በመንፈስ ቅዱስ ምሪት አማካይነት በተጻፉት ቅዱሳት ምስክርነት ላይ ነው። የሐዋሪያት ምስክርነት እስከ ክርስቶስ ዳግም ምጸት ድረስ የጸና ነው። ስለዚህም ከቀኖና መዘጋት በኋላ አዲስ መሠረት ለመጣል መሞከር ሌላ ዓይነት አካልን እንጂ ቤተክርስቲያንን የሚወክል አሠራር አይሆንም። እንዲህማ ከሆነ ቅዱሳት መጻህፍትም አያስፈልጉንም፤ ተጽፎ የተላለፈልንም የሐዋሪያት ምስክርነት ዋጋ አይኖረውም ማለት ነውና ቤተክርስቲያን ልትቀበለው አትችልም፤ ነገሩም ከነመሰረቱ የተሳሳተና በዘመን መጨረሻ ላይ በድንቅና በተዓምር ብቻ የሚመራ እውነትንና ህይወትን ያላወቀ የህዘብ ስብስብ በመፍጠር ቤተክርስቲያንን ለማሳሳት የተፈጠረ ነውና ብርቱ ጥንቃቂ ያሻል።

## ነቢያትና ትንቢት የመናገር አገልግሎት
## (ትንቢታዊ መልእክት የማስተላለፍ ሥጦታ)፡-

25. የጸጋ ሥጦታ ልዩ ልዩ ነው፤ አገልግሎቱ ግን ለአንዷት የክርስቶስ አካል ነው። በዚህ አጭር ጽሑፍ ውስጥ የጸጋ ሥጦታዎችን ሁሉ በዝርዝር ማቅረብ አይቻልም። ይሁን እንጂ አሁን ባለንበት ዘመን በአቢያተ ክርስቲያናት ከሚከሰቱት ፈርጀብዙ መንፈሳዊ ቀውሶች አንዱ ትንቢታዊ መልእክት የማስተላለፍ ሥጦታ ስለሆነ እሱኑ በአጭሩ እንመለከታለን። በዚህ ጽሑፍ የትንቢት ሥጦታ የሚለውን የማንጠቀመው የነቢያት አገልግሎት መደብ አለመኖሩን ለማመልከት ነው። እንደገናም ትንቢታዊ መልእክት የማስተላለፍ አገልግሎት የቃሉንም ስብከትና ትምህርት የሚጨምር እንጂ እግዚብሔር እንዲህ ይላል በሚል አኳኋን ላይ ብቻ አለመወሰኑን ለማመልከት ነው።

26. በብሉይ ኪዳን አነጋገር ነብይና የነብይነት ኣገልግሎት በተናጠል ይታያሉ። ነቢይ ኣገልጋዩን ሲሆን ነብይነት ኣገልግሎቱን ይመለከታል። ነቢያት የተነበዩለት፣ ለማየትም በጉጉት የጠበቁት በሰው ታሪክ ገብቶ የኖረና ያገለገለ የነቢያት ትንቢት ሁሉ ፍጻሜ የሆነ ታላቁ ነብይ ከገሊላ ናዝሬት የመጣው *"ነብዩ ኢየሱስ"* እንደሆነ ቅዱሳት መጻሕፍት መስክረዋል። ክርስቶስም ነቢይ በገዛ ኣገሩ እንደማይከበር ሲናገር የነቢይነቱን አገልግሎት ነበር ያረጋገጠው (ማቴ 13: 57)።

27. በኣዲስ ኪዳን ትንቢታዊ መልእክት የማስተላለፍ ሃላፊነትም ሆነ ተጠያቂነት የቤተክርስቲያን ነው፤ መልእክቱን የሚያስተላልፉት ግለሰብ ምእመናን ሊሆኑ ይችላሉ፤ አገልግሎቱ ግን የቤተክርስቲያን ነው። ስለዚህ ቤተክርስቲያን የተላለፈውን ትንቢታዊ መልእክት መፈተሽና ከመንፈስ ቅዱስ ከሆነ የራስዋ መልእክት እንደሆነ አድርጋ ኃላፊነቱን መቀበል፤ ካልሆነም በይፋ ማውገዝ ግዴታዋ ነው። አገልግሎቱም የሚሰጠው በግለሰቦች ብቃት ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ በሚሰጣቸው ሃይልና ሥጦታ ነው። አገልግሎቱም ስጦታውን በተቀበሉት ግለሰቦች ውሳኔ ወይም ፕሮግራም ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ ራሱ በመረጠው ጊዜ፣ ሁኔታና ቦታ ነው።

28. ከነቢያት መካከል በቀዳሚነት የሚታወቀው ሙሴ ሲሆን፣ በኋላም እንደነ ኤልያስ፤ ኢሳይያስ፣ ኣሞጽ፣ ሆሴዕ፣ ኤርምያስና የመሳሰሉት ታዋቂ የብሉይ ኪዳን ነቢያት ተነስተው ነበር። የእነርሱም ነቢይነት ፍጹም ወደ ሆነው "ከገሊላ ናዝሬት ወደሆነው ነብዩ ኢየሱስ" ማመልከት ስለነበረ፤ አሁን የእነርሱ ዓይነት ነቢይ አይነሳም ወይም የለም አያስፈልግምም (ዘዳግ 18:15)። ሕግም ለወንጌል ሞግዚት ሆኖ

እንዳገለገለ፣እንዲሁ የብሉይ ኪዳን ነቢያት ቃል ወደ ኢየሱስ ሲደርስ ዓላማው ፍጻሜ አግኝቷል። ለዚህ ነው መጥምቁ ዮሐንስ ከታላላቅ የብሉይ ኪዳን ነቢያት የመጨረሻው ተብሎ የሚጠቀሰው።

29. ይህን ስንል በአዲስ ኪዳን የትንቢት አገልግሎት ቆሟል ማለታችን እንዳይደለ ልብ ሊባል ይገባል። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በጸጋው ኃይል በወደደው መንገድ ሳያቋርጥ በየጊዜው *በቤተክርስቲያን ለቤተክርስቲያን* ትንቢዊ መልእክት ስለሚሰጥና ልዩ የትንቢት አገልግሎት ላይ ብዙ ማተኮር እንደማያስፈልግ ለማመልከት ነው። በተጨማሪም "በቀደመው ዘመን እግዚአብሔር ለአባቶቻችን በነቢያትና በተለያዩ መንገዶች ቢናገርም በዘመን መጨረሻ ለምንኖር ለእኛ በልጁ በኢየሱስ በኩል ፈቃዱን ገልጦልናልና" የሚለው ሐዋሪያዊ ምክር በክርስቶስ በኩል ለተገለጠው እውነት ብቻ እንድንታዘዝ ስለሚያመለክተን ነው (ዕብ 1)። የጥንቷም ቤተክርስቲያን በኢየሱስ ነቢይነት የነቢያት ሁሉ ትንቢት ፍጻሜ ማግኘቱን መስክራለችና (የሐዋ 3:22 _ 23፣7:37)።

30. ከኢየሱስ ለመማር ይከተለው የነበረው ሕዝብም እርሱን እንደ ነቢይ ተቀብሎት እንደነበረ ከወንጌላት እንማራለን (ማቴ 16: 14፣ 21:46፣ ሉቃ 7:16)። ለዚህም ከእናቱ ማህጸን ጀምሮ ዓይነ ሥውር የነበረ፣ በኢየሱስ እጅ ከተፈወሰ በኂላ *"እርሱ ነቢይ ነው!"* በማለት የሰጠው ምስክርነት ለኣብነት ሊጠቀስ ይችላል (ዮሐ 9)። በእግዚአብሔር ዘንድ ቃል የነበረ፣ በኂላም ሥጋ በመልበስ ጸጋና እውነትን ተሞልቶ በሰዎች መካከል በመገኘት እግዚአብሄር ኣብን የገለጠልን እርሱ ነውና (ዮሐ 1)።

31. በመጨረሻው ዘመን ለምንኖር ለእኛ ደግሞ ነቢያት ራሳቸው ትንቢት እየተናገሩለት፣ራሳቸውም ሊያዩት ይናፍቁ የነበረ፣ እግዚኣብሔር ለእኛ የተናገረበት የመጨረሻ መልዕክትና መልዕክተኛው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። "እርሱን ስሙት" የሚለው ከኣብ ዘንድ የመጣው ቃል ኢየሱስ በሥጋ የተገለጠ የእግዚኣብሔር ጥበብ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል(1 ቆሮ 1:30)። ሙሴ በትንቢት "እርሱን የማትሰማ ነፍስ ትጠፋለች" ያለው እርሱ የእኛ ነቢይ መሆኑንና እርሱን ብቻ እንድንሰማ እንደብሉይ ኪዳን ነቢያት በትንቢት ተስፋ የምንኖርበት ጊዜና ዘመን ኣይደለም። የእነርሱ ትንቢት እንደሞግዚት ሆኖ ወላጅ እስኪመጣ ይጠብቅ ነበርና። ኣሁን ግን በክርስቶስ በኩል የተሰወረው የእግዚኣብሔር ጥበብ ተገልጧልና (ቆላስ 2:3)።

32. ከላይ እንዳወሳነው የጥንቱ ነቢያት መልዕክቶቻቸውን የሚቀበሉት ከጠራቸው እግዚአብሄር ከራሱ በቀጥታ ነበር (ዘጸ 3:1-4፤ኢሳ 6:6-8)። በኣንጻሩም ሥልጣንንና ክብርን በመመኘት ሐሰተኛ ነቢያት በራሳቸው ሥልት ወደ ነቢይነት ቦታ ወይም ኣገልግሎት ሰግስገው ራሳቸውን ያስገቡ እንደነበረ ቅዱሳት መጻሕፍት በግልጽ ያስረዳሉ (ኤርም 14:14፤23:21)። ነቢያት በሰዎች ፊት ቆመው ሲናገሩ በእግዚአብሔር ፊት እንደቆሙ ይቆጠራል (1 ነገሥ 17:1፤ 18:15)። ነቢያት በራሳቸው ፍላጎት ሲሾሙ ወይም ራሳቸውን ሲሾሙ ማየት መጽሓፍ ቅዳሳዊ አለመሆኑን ማንም ቅንጣት ያህል ሊጠራጠር ኣይገባም። እግዚኣብሔር እነ ሙሴን ፤ ኤልያስን፤ ኤርምያስን ፤ ኣሞጽንና ዮናስን ሲጠራ ጥሪውን ላለመቀበል መከራከራቸው ፈቃደኛ ካለመሆን አልነበረም። ነገር ግን አገልግሎቱ ታላቅና በኃላፊነት የሚያስጠይቅና እነርሱም በራሳቸው ከራሳቸው የሆነ ብቃት የሌላቸው መሆናቸውን በመገንዘባቸው ነው።

33. ከአገልግሎታቸው መካከል የሚበዙቱ ነገሥታትን እስኪፈታተኑ ድረስ ስለፍትህ መጓደል በገሃድና በኣደባባይ የወቀሳና የማስጠንቀቂያ መልእክት ማስተላለፍ ነበር። ለዚህም ነቢዩ ናታን ንጉስ ዳዊትን ከኦርዮን ሚስት ጋር ስለማመንዘሩ፣ እንዲሁም መጥምቁ ዮሓንስ በዘመኑ የሮም ተወካይ የነበረውን የይሁዳ ኣገረ ገዥ ሄሮድስን የወንድሙን ሚስት ስለመውሰዱ ማውገዙ ለኣብነት ሊጠቀሱ ይችላሉ ። ይህንና ይህንን የመሳሰሉት ኣገልግሎቶች መስጠታቸው ነቢያትን ተወዳጆች ሳይሆኑ ተሰዳጆች አድርጎኣቸዋል። አንዳንዶች መከራቸው ሞትን እስኪመኙ ድረስ ኣንገሽግሾኣቸዋል። እውነትን በእውነትና በፍጹም ቅድስና በድፍረት ፊት ለፊት ተናግረዋልና፤ በጊዜያዊ ድለላና ጥቅም አልተረቱምና። ነቢይ በመሆናቸውም ከተገልጋዩ ህዝብ ልዩ ክብርና ሪብ አልጠበቁም።

34. ስለዚህ ከብሉይ ክዳኑ ታሪክ እንደምንረዳው ነቢይነት ግለሰቦች ፈልገው የሚቀበሉት አገልግሎት ሳይሆን እግዚአብሔር በፈለገው ጊዜና ለፈለገው ሰው ለመንግስቱ አገልግሎት ሲል የሚሰጥ ነበር፡፡ የጥንቱ ነቢያት አገልግሎት በእርግጥ ማህበራዊና ብሄራዊ ነክ ጉዳዮችንም ጭምር ይዳስስ ስለነበረ ነገሥታት ሳይቀሩ ይፈሩአቸው፣ ይጠሉአቸውና፣ ያሳድዱአቸው እንደነበር የነቢያት አገልግሎት ታሪክ ይመሰክራል፡፡ ዛሬም ቤተ ክርስቲያን ትንቢታዊ መልእክት የማስተላለፍን አገልግሎት ከቤተ ክርስቲያን ግድግዳዎችና ከምዕመናን መንፈሳዊ ሕይወትና ሥጋዊና ማህበራዊ ብልጽግና ባለፈ መልኩ በማህበረሰብና በአመራር ባሉት ደረጃ ዘልቆ እንዲሰማ ጥረት መደረግ አለባት፣ ማህበራዊና ብሔራዊ ነክ ጉዳዮች የእግዚአብሔር ጉዳዮች ናቸውና፡፡ ሙስና በሰፈነበት፣ ሥልጣንን ያለአግባብ መጠቀም በበዛበት፣ የደካሞች መብት በተረገጠበት ጊዜና ቦታ ሁሉ ቤተክርስቲያን ትንቢታዊ ድምፅዋን ማሰማት ይጠበቅባታል ፤ ጥሪዋም ነው፡፡ ነገር ግን ቤተክርስቲያን በብሉይ ክዳን ዘመን እንደነበረው ዓይነት ነቢያትን መድባ ለመንግስታትና ለህዝቦች ትንቢት እንዲናገሩ አታሰማራም፡፡ ራስዋ ቤተክርስቲያን ትንቢታዊ ቃል አላትና በሚመቻት መንገድ ሁሉ ትንቢታዊ ድምጽዋን ታሰማለች፡፡

35. እዚህ ላይ ልብ እንበል፣ አሰራሩና አደራረጉ የመንፈስ ቅዱስ ቢሆንም በተለየ መልኩ ትንቢታዊ መልእክት የማስተላለፍ ሥጦታ ያላቸው ምእመናን አሉ፡፡ መልእክቶቻቸው መጽሐፍ ቅዱስን መሰረት ያደረጉና ቤተክርስቲያንን ለማነጽ የሚጠቅሙ፣ ለግለሰቦች እና ለግል ጉዳይ ያልሆኑ መሆን አለባቸው(1ቆሮ 14፡1-2)፡፡ በርግጥ ለግለሰቦች ትንቢታዊ መልእክት ሊመጣ ይችላል፣ ግን የዚያ መልእክት ዓላማና ግብ ቤተክርስቲያንን የሚመለከት መሆን ይገባል፡፡ በጥንትዋ ቤተክርስቲያንም ትንቢታዊ መልእክት የማስተላለፍ አገልግሎት የነበራቸው እንደነአጋቦስን እንመለከታለን (የሐዋ 21፡10፤ ፡፡ ለምሳሌ አጋቦስ ለጳውሎስ ያስተላለፈው መልእክት ዋና ግብ ወንጌል ነበር፣ የቤተክርስቲያን ጉዳይ ነበር፣ ጳውሎስ ዋነኛው ባለጉዳይ አልነበረም፡፡ እንደቤተክርስቲያን አገልጋይ በህይወቱ ሊከሰት ያለውን ለማመልከትና ለዚህም ዝግጅት እንዲያደርግ ለማሳሰብ የተላለፈ መልእክት ነበር፡፡ በርግጥ በሐዋሪያት ስራ የነቢያት ስም ተጠርቶአል፡፡ ይህ ግን በአዲስ ኪዳን የነቢያት የአገልግሎት መደብ ለማመልከት የተሰጠ አጠራር ሳይሆን በጊዜው ቤተክርስቲያን ገና ከአይሁድ ስርአት ጋር በተያያዘ አሰራር ውስጥ እያደገች ስለነበር ከልምድ ጋር የተገናኘ አጠራር ነው፡፡ በሄሌኒስቲኩ ዓለም ( በግሪኩ) የባእድ አምላኪዎች በልዩ መንፈሳዊ መገለጥ የሚናገሩ ( የክርስቲያኑንም ጨምሮ) ነበሯቸው፣ እነዚህም ነቢያት ይባሉ ስለነበር(የሐዋ 13፡6) የነአጋቦስ ነቢይ ተብሎ መጠራት አያስገርምም፣ በአዲስ ኪዳን የነቢይነት አገልግሎት መደብ መኖር ይገባዋል ለሚለው ክርክርም እንደማረጋገጫ ሊጠቀስ አይችልም፡፡

## <u>የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን አቋም</u>

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ በምእመናን ሁሉ ክህነት ታምናለች፡፡ ስለዚህም በሐዋሪያትና በነቢያት ምስክርነት ላይ በጸና እምነት የሚኖሩት ሁሉ አፖስቶሎስ ( መልእክተኞች ) እንደሆኑ ታምናለች፣ አገልግሎትዋንም በዚሁ አኳኋን ትመራለች፡፡ በዚህና ከላይ በተዘረዘሩት መጽሐፍ ቅዱሳዊና ሥነመለኮታዊ እይታ ላይ በመመስረት ቤተክርስቲያኒቱ በሚከተለው መልኩ አቋምዋን ይፋ ታደርጋለች፡፡

### ሀ. <u>ስመተ-ሐዋሪያን በሚመለከት (Apostolic Office and Title)</u>

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ እንደሉቴራዊነትዋ "ሐዋሪያ" የሚለው ሹመት የክርስቶስን ሞትና ትንሳኤ በታዘቡትና በክርስቶስ ቀጥታ በተሾሙና በሐዋሪያዊ ምስክርነታቸውም ቤተክርስቲያንን በመሠረቱ የመጀመሪያዎቹ ሐዋሪያት የተገደበ መሆኑን ታምናለች፡፡ ስለዚህም የዘመኑን ሲመተ ሐዋሪያት እንቅስቀሴ የተሳሳተ እንቅስቃሴ ከመሆኑም በላይ ቤተክርስቲያንን ግራ የሚያጋባ አካሄድ መሆኑን ታረጋግጣለች፣ አካሄዱን አትቀበልም፣ ከእንቅስቃሴው ጋር ግኑኝነት ካላቸው አካላት ጋርም አትተባበርም፡፡

## ለ. “የነቢይነት መደበ አገልግሎት ወይም ሲመተ ነቢይ ( Office of Prophecy)

የነቢይነት ሹመት በቢሉይ ኪዳን ዘመን የነበረና መሲህ የሆነው ክርስቶስ ወደዓለም በመምጣቱ ያበቃ የአገልግሎት ሹመት እንደሆነ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ ትገነዘባለች፤ እንዲሁም ትንቢት ሁሉ በቅዱስ ቃሉ የተጠቃለለና ከሐዋሪያትና ከነቢያት የተላለፈው ምስክርነት በቂ መሆኑን ታረጋግጣለች። ይሁን እንጂ ቃሉን መሠረት ያደረገና እውነተኛነቱ የሚያስተማምን ትንቢታዊ መልእክት ለቤተክርስቲያን መታነጽ እስከጠቀመ ድረስ አገልግሎቱን ትቀበላለች፤ ነገር ግን አገልግሎቱን እንጂ መደበ አገልግሎቱን ወይም ስያሜውን አይደለም፤ የአገልግሎቱም አደራረግ በቤተክርስቲያኒቱ ሥርዓት ውስጥ መጠበቅና በ1ቆሮ 14 በተዘረዘረው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያ መሆን እንዳለበት በአጽንኦት ታሳስባለች።

በኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ ሥራ አስፈጻሚ ቦርድ
17ኛው ስብሰባ
አዲስ አበባ ታህሳስ ---2003

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን
መካነ ኢየሱስ
1
The Ethiopian Evangelical Church
Mekane Yesus